Finote Ethio-Canadian Information Centre In Toronto
ፍኖተ ኢትዮ-ካናዳውያን የኢንፎርሜሽን ማዕከል በቶሮንቶ
1910 Kennedy Road, Unit 3, P. O. Box 417, Toronto, ON, M1P 2L8 E-mail: torontofinote@gmail.com

# ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት ዛሬም የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀዳሚ ጥያቄና ለሀገራችን የፖለቲካ ችግር ብቸኛ መፍትሔ ነው!

ከአደሜ ቢላል

## መግቢያ

የአንድ ሀገር ሉዓላዊነትና  እና ሕዝባዊ መንግስት የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው።የኢትዮጵያ ሕዝብ ዋነኛው ጥያቄው የዲሞክራሲ ጥያቄ ነው፡፡ ዲሞክራሲን ማስፈን ማለት ሕዝብ የሚገዛበት ፍትሐዊ ነጻ አገዛዝ ወይም በሕዝብ የተመረጠን ሕዝባዊ መንግስት መመስረት ማለት ነው፡፡ እስከዛሬም በኢትዮጵያ የመንግስታዊ  ታሪክ ውስጥ በሕዝብ የተመረጠ መንግስት ኖሯት አያውቅም፡፡ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከ 1966 አስከ አሁን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ልጆቹን የገበረው ሕዝባዊ ስርዓትን ለማምጣት ሲሆን ትግሉ አሁንም ድረስ ቀጥሎ ይገኛል፡፡ በሕዝብ ያልተመረጠ መንግስት ደግሞ አምባገነን ነው፡፡ አምባገነን መንግስት ደግሞ በራሱ ፍቃድ አንድን አገር ወደ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ሊወስድ አችልም፡፡ ምክንያቱም አምባገነን በራሱ ፍቃድ ራሱን ሊያጠፋ አይፈልግምና፡፡ ለዚህም ነው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ  በገዢው ፍቃድ ዲሞክራሲ እደማያገኝ ስለሚያውቅ ከ1966 ጀምሮ የሚከተሉትን የዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎችን በማንሳት ትግሉን ያፋፋመው፤ ጥያቄዎቹውም መሬት ላራሹ፣  ዲሞክራሲ ለሰፊው ሕዝብ ያለገደብ፣ ሕዝባዊ የሽግግር መንግስት ወዘተ በማለት  ሲታገል እጅግ ብዙ መስዋዕትነት ከፍሎበታል፤ አሁንም ትግሉና መስዋዕትነቱ እደቀጠለ ይገኛል፡፡

### ሕዝባዊ መንግስትን ለመመስረት በሚደረገው ትግል ላይ የነበሩና ያሉ ጋሬጣዎች

1. የኢትዮጵያ ሕዝብ በ 1966 ሕዝባዊ አመጽ የነበረውን ንጉሣዊ ስርዓት ገርስሶ በተስፋ የጠበቀውን የሕዝብ መንግሥት ለመመስረት አሽጋጋሪ የሚሆነውን ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ለመመስረት ባለመታደሉ፣ አጋጣሚውን ተጠቅሞ ወታደራዊ ክፍሉ በወቅቱ የነበረውን ጸጥታ ለማስከበር ከካምፑ ወጥቶ ራሱን ‘የጦር ኃይሎች የፖሊስና የብሄራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ’ በማለት የሃገሪቱን ጸጥታ አስከብሬ ሕዝባዊ መንግሥት ተመስርቶ ወደ ካምፕ እመለሳለሁ ብሎ ቃል ከገባ በኋላ ቀስ በቀስ ስልጣኑን በማደላደል ‘የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ’ በማለት የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄን ውድቅ በማድረግ በወታደራዊ አምባገነንነት አገዛዙን በመቀጠሉ ከሕዝብ ጋር ተራርቆ ህዝባዊ መንግሥት ጥያቄን እንዳይነሳ ህዝብን በመጨፍጨፍ፣ በማሰርና በማሳደድ ፍጹም አምባገነን ሆኖ ቀጠለ። ቀጥሎም እራሱን ‘የኢትዮጵያ ሠራተኛ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚሽን’ አድርጎ ወታደራዊ አገዛዝ አድር ባይ ምሁራንን በመያዝ ዩኒፎርሙን በሲቪል ልብስ ቀይሮ አገዛዙን በማጠናከር በመጨረሻም ‘የኢትዮጵያ ሠራተኛ ፓርቲ’ ሆኛለሁ ብሎ በፍጹም ወታደራዊ አምባገነንነት እነ ኮሎኔል መንገሥቱ ለ17 ዓመት በጭካኔ በመግዛት አንድ ትውልድ አጥፍቶና አሰድዶ፣ ሀገራችንንም ለከፍተኛ አደጋ አጋልጦ በራሱ ጥፋት ተንኮታኩቶ ወደቀ።

2. የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄ ቢዳፈንም የወያኔ ሰርዓት በብሔረሰብና በዘር ተደራጅቶ ሲመጣ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ሰብዓዊ መብት የሚከበርበት፣ ሁሉም በቋንቋውና በባህሉ እኩል የሚሆንበት፣ በዲሞክራሲያው መንገድ ከሕዝብ የተውጣጣ ጌዜያዊ የሽግግር መንግሥት ተመስርቶ ሀገራችንን ማዳን የሚቻልበትን ሁኔታ እንዲቀበር ያደረገው የሻዕቢያ፣ ወያኔና አነግ ዓላማና አደረጃጀት ጸረ ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ኢትዮጵያዊ አጀንዳ ያነሳውን ሁሉ እያፈኑና እያጠፉ ዓላማቸውን እውን ለማድረግ የጎሳ ፖለቲካን በማራመድና ኢትዮጵያዊነትን በመናድ መንገዳቸው ገፉበት። ላላፉት 29 ዐመታት እጅግ ብዙ ወንጀሎች በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያዊነት ላይ ተፈጸሙ። ከፍተኛ  ጄኖሳይድ በተለይ በአማራው ላይ ተካሄደ፣ በአኝዋክ ብሄርሰብ ላይ ተፈጸመ፣ ኢትዮጵያዊነት ወንጀል ሆኖ ብዙዎች ተገደሉ፣ ታሰሩ፣ ተሰደዱ፣ አካለ ስንኩል ሆኑ ከመሬት በታች በጨለማ እስር ቤቶች ፍዳቸውን አዩ፣ ቅርስ ጠፋ፣ የህዝብ ሀብት ተዘርፎ ወደየውጭ አገሮች ባንኮች ኮበለለ፣ ህዝብ ተወልዶ ባደገበት አገር ተፈናቀለ፣ ተሰደደ፣ በአጠቃላይ ምን ያልተደረገ የጥፋት ስራ ተሰራ ማለቱ ይቀላል። ባንጻሩም ክልል ተበጅቶ  ህዝብን እንደ ከብት መከለልና ማጎር የስርዓቱ ዋነኛ መገለጫና ስራ ሆነ። ዋናው ዓላማም የህዝብ አንድነትን መናድ እና በቋንቋ ከፋፍሎ ማጋጨት፣ ጥላቻን መስበክ፣ በሃገሩ ሁለተኛ ዜጋ አድርጎ እንዲኖር በማድረግ የህወሓትን ዘረኛ አገዛዝ ማራዘም ነው። አገርን ማስገንጠል እንደታላቅ ድል ተቆጥሮ ሕዝብን አለያይቶ ሲያበቃ አገራችንን ወደብ አልባ አድርጎ አስቀራት። ለዚህ ስርዓት እድሜ የውጭ አገራት ከፍተኛ ድጋፍና እርዳታ ትልቅ ሚና በመጫወቱ ትግሉን ወስብስብና አዳጋች ማድረጉ ሳይነሳ የማይታለፍ ነው። የኢትዮጵያ ጠላቶች ሁሉ በየፊናቸው በገንዘብ ኃይል ጀሌዎቻቸውን በማደራጀትና በመርዳት ብዙ ጥፋቶችን አደረሱ፣ ባህላችን በውጭ ጎጂና አጥፊ ባህል በስልጣኔና በፋሽን ስም እየተለወጠ ትውልድ የአደገኛ ሱስ ስለባና ወንጀል ፈጻሚ እንዲሆን ከፍተኛ ስራ ተሰራ። የሃይማኖት መከባበርና ተቻችሎ መኖርን በአክራሪዎች ወደ ግጭቶች እንዲያመራ አደገኛ ስራ ተሰራ፣ ሰርዐተ ትምሕርቱ ደረጃውን በማውረድ በተማረ ትውልድ ስም ብዙ ‘የተማሩ’ ማህይሞችን ፈጠሩ።

27 አመት የወያኔ አገዛዝ በሳተላይት ድርጅቶች አማካኝነት ኢትዮጵያ ላይ የፈጸመው ወንጀል ግፍና ሰቆቃ ሞልቶ በመፍሰሱ ሕዝባዊ አመጽ በየቦታው በመነሳቱ አገዛዙ ለመቀጠል ባለመቻሉ፣ የሕዝብ ኃይል እያየለ ሲመጣና ሊወድቅ አንድ ሀሙስ ሲቀረው አገዛዙን ለማዳን በለውጥ ስም አንድ ቡድን ከኢሃዴግ ብቅ በማለቱና 'የለውጥ ነፋስ' የመጣ በማስመሰል ስርዓቱን በሌላ መልክ ለማስቀጠል የተቀነባበረ ድራም ከግሩም ተዋናይ ጋር ድንገት መጣ። አንዳንድ መሻሻሎችን በማሳየት የሕዝብን ድጋፍ ለማግኘት ሕዝብ የናፈቀውን ኢትዮጵያ የሚለውን ቃልና ኢትዮጵያዊነትን ደጋግሞ በመጥቀስና ቃል በመግባት ብዙ ኢትዮጵያኖች 'ሀገሪቱ' የሚለውን ቃል በኢትዮጵያዊነት በመተካቱ፣ እስረኞች በከፊል በመፈታታቸው ተቃዋሚውም ከውጭ እንዲገባና ከየበረሃው እንዲመለስ ጥሪ በማድረግ የማይታመን ድራማ ተሰራ። ተዋናዮቹ ለ27 ዓመታት ህዝብን ሲገድሉ፣ ሲያስገድሉ፣ ሲሰልሉ፣ ሲያስሩ፣ ሲያሰድዱ የነበሩ የሰርዓቱ አካሎች ናቸው እንጂ ስር ነቀል ለውጥ ሳይመጣ 'የለውጥ መጣን' ነጠላ ዜማዎች ለቀቁ፣ ነጋሪት አስመቱ፣ ህዝብን 'ተንፍስ' ብለው ሲተነፍስ ቁጣውን ቀዝቃዛ ውሃ ቸለሱበት። የለም አካሄያዳችሁ አላማረንም ብለው ሊቋቋማቸው ያሰበውንና የተነሳውን ሁሉ በተለመደ ሴራቸው ባጭሩ ቀጬት ለዚህም አንድ ምሳሌ ብቻ ብጠቅስ የሰኔ 15ቱ የነጄኔራል አሳምነው ጽጌ ግድያ በቂ ማስረጃ ነው፡፡

3. የሽግግር መንግሥት ጥያቄ በአንድ የወያኔ ስርዓት ወልዶ፣ አሳድጎ ያጎለመሰው ለስርዓቱ ታማኝ ሆኖ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ስንት የጥፋት ስራ የሰራን ሰው ዛሬ የሕዝብ አመጽ ሲያስበረግጋቸው፤ ኢህአዴጎች ተሰባስበው የመረጡት ጠቅላይ ሚኒስትራቸው 'እመኑኝ የሽግግር መንግስት አያስፈልግም፣ እኔው አሽጋግራችኋለሁ' ብሎን እርፍ! እንዴት ተቀለደብን ጃል። ከመቶ ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ያላትን ሀገር አንድ ሰው እኔው አሸጋግራችኋለሁ ሲል ጥያቄው ገብቶት ነውን? ወይስ የሽግግር መንግሥት ምን እንደሆነ ሕዝብ አያውቅም ማለቱ ነው ያስብላል።

<u>**የሽግግር መንግሥት እንዴት? ለምን? በማን? ለምን ያህል ጊዜ ይመሰረታል?**</u>
<u>**ኃላፊነቱስ ምንድነው? እነዚህን ጥያቄዎች አጠር ባለ መልኩ እንድሚከተለው ቀርቧል፡፡**</u>

ኢህአዴግ የዘረኛና አምባገነን አገዛዝ መገለጫ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን ጸረ ዲሞክራሲና ጸረ ኢትዮጵያ የሆነውን የኢህአዴግን/ብልጽግና ሕገወጥ አገዛዝ ለመተካትና የሕዝብ ስልጣን ምንጭነትና ባላቤትነት መንገድ ጠራጊ የሆነውን የሽግግር መንግስት መቋቋም አማራጭ የማይገኝለት ዘላቂና አስተማማኝ መንገድ ነው፡፡ ስለሆነም የሽግግር ዐቢይ ዓላማ፤ የአገሪቱ የወደፊት ዕድል በአንድ ነፍጥ በታጠቀ የፖለቲካ ቡድን እጅ በድጋሚ እንዳይወድቅ ለማድረግ ወሳኙና አድራጊ ፈጣሪው ሕዝብ ብቻ መሆኑን ያረጋግጣል።

1. የሽግግር መንግሥት የሚመሰረተው፣ በሽግግሩ መንግስት ለመሳተፍ ፈቃደኞች ከሆኑ የፖለቲካ ኃይሎች፣ ከሕብረተሰብ ወኪሎች፣ ከሠራተኛ ማህበራት ተጠሪዎች፣ ከሃገር ሽማግሌዎች ፣ ከታዋቂ ግለሰቦች ፣ ከምሁራን፣ ከሴቶችና ከወጣቶች ማህበራት ተወካዮች ወዘተ... የተውጣጣ የሽግግር መንግስት ተመስርቶ በአገር አቀፍ ምርጫ ለሚቋቋመው የሕዝብ መንግስት ጥርጊያ መንገድ ለማዘጋጀት ነው።

2. የሽግግር መንግሥት፤ ከሽግግር መንግሥት ጠቅላላ ጉባኤ ምክር ቤት በመመስረት፣ ምክር ቤቱ የሚመራበትን ደንብ ያዘጋጃል፣ የሽግግር መንግሥትና አስተዳደር ይመሰርታል። ምክር ቤቱም በሽግግር ወቅት ከፍተኛው የመንግስትና የአስተዳደር እርከን ሆኖ ሀገሪቱን የሚያስተዳድር አካል ይሆናል፡፡

3. አገር አቀፍ የሰላምና የእርቅ ኮሚቴ በመመስረት በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በህዝብ ውስጥ በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የተፈጠረው ቁርሾ በስምምነት፣ በፍቅርና በሰላም እንዲያልቅ በማድረግ በአገሪቱ ውስጥ ከዚህ በፊት፣ በሆኑና ወደፊት በሚሆነው ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት እንዲደረግ የውይይት መድረኮችን ያዘጋጃል፤

4. የሽግግር መንግሥቱም የተለያዩ አካላትን በማዋቀር ጥርጊያ መንገዱን ያስተካክላል፤ ለምሳሌም በሙያው፣ እውቀቱና ብቃት ባላቸው ባለሙያዎችና የህግ ሰዎች የተካተቱበት የህገ መንግሥት አርቃቂ አካል(ኮሚሽን) በማስመረጥ፣ ሁሉንም ዜጋ ያሳተፈ፣ ህዝብ የተወያየበትና የመከረበት እንዲሁም ያጸደቀው ሕገ መንግሥት ይቀርጻል፣ የሀገሪቱ ህግ ሆኖ እንዲተገበር ያደርጋል፡፡

5. ከህዝብ የተውጣጣ እውቀቱና የስራ ልምድ ያላቸው ነጻ የምርጫ ቦርድ አካል በመፍጠር የወደፊቱን ሕዝባዊ መንግሥት ያለምንም ተጽዕኖ እና ጣልቃ ገብነት እንዲያካሂድ ያዘጋጀል፡፡

6. በሕገመንግስቱ ውስጥ የሕግ አውጪው ፣ የሕግ አስፋጻሚውና የዳኝነት ሰጪው መንግስታዊ ዘርፎች ስልጣናቸው፣ ኃላፊነታቸውና ተግባራቸው በግልጽ ተለይቶ መቀመጡን ያረጋግጣል፤

7. ነጻ የሕዝብን ድምጽ የሚያስተጋቡ፣ በመንግሥት ተጽዕኖ የመንግሥትን ፕሮፓጋንዳ ብቻ በማሰማት ህዝብን የማያደነቁሩ፣ ሁሉንም የህበረተሰብ ክፍሎች በእኩል የሚዲያ ሽፋን እና ሰዓት አገልግሎት የሚሰጡ ነጻ የሚዲያ ተቋማት ሊኖሩ ይገባል፡፡

በሚያቀርቡትም የዜና ሽፋን ወይም ዝግጅት ማስፈራሪያ፣ ማሸማቀቅ፣ እስራትን ሊሎችም ለስራቸው እንቅፋት የማይፈጠርበት ሁኔታ መፈጠር ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

በሕገ መንግስት ውስጥ የኢትዮጵያ ሀገር ወሰንና አገራዊ ሉዓላዊነትና ድንበሮቿዋም የማይደፈሩና የማይገሰሱ መሆናቸው መጠቀሱን ያረጋግጣል፤ በሕገ መንግስቱ በሕዝብ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ የሚቋቋመው ምክር ቤት ሕግ አውጪ ዘርፍ ባለ ሁለት ክፍሎች እንደሆነና አንደኛው ክፍል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአስተዳደር አካባቢዎች ከሕዝብ ብዛት ላይ የሚመሰረት፣ ሁለተኛው ክፍል በፌዴራል የብሔረሰብ ስብጥር ላይ ተመስርቶ ሁሉም ብሔረሰቦች በዕኩል የሚወከሉበት ሆኖ ፣ የሁለቱም ክፍሎች አባላት በቀጥታ ከህዝብ የሚመረጡ መሆናቸው መገለጹን ያረጋግጣል፤ የተለያዩ የመንግሥት አካላት ሥራቸውን በሚገባ መሥራታቸውን የሚቆጣጠር የቁጥጥር አካል ስይሞ የሽግግሩን ሂደት በንቃት ይቆጣጠራል.።

- የሕግ የበላይነት በተግባር መዋሉን ያረጋግጣል፤
- የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ሕዝብ የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን ያለተጽዕኖ ለሕዝብ እንዲያስተዋውቁ ያደርጋል።
- መከላከላያ ኃይሉ የሀገሪቱ ሰላምና ዳር ደንበር ከመጠበቅና በተመደበበት መስክ ከመስራት በቀር በመንግሥት ደጋፊነት ወይም የፖለቲካ ጉዳይ ወስጥ ጣልቃ እንዳይገባ ትምህርትና ስልጠና ይስጣል፣ በህግ ይወሰናል።
- የፍትሕ፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የመንግሥት አገልግሎት፣ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ፣ የንግድ፣ የባህል፣ የእምነት ተቋማት፣ የወጣቶች፣ የመከላከያ ኃይል፣ ወዘተ... ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት እጅግ ወደ ኋላ ከቀረንበት ደረጃ በጥቂት ዓመታት ወስጥ እድገት የሚያሳዩበትን ፖሊሲ ይቀርጻል።
- የሽግግር መንግሥቱ የሕዝቡን ዲሞክራሲያዊ መብቶችን አክብሮና አስከብሮ ይሰራል።
- የሀገሪቱን ደህነነት ሳይሆን የኢህአዴግ/ብልጽግና ሥልጣን ዘመኑን ለማራዘም የተቋቋሙ ልዩ ኃይሎችና ተቋሞች በሙሉ ይፈርሳሉ።
- የሽግግር መንግሥት የሥልጣን ዘመን ከሁለት እስከ ሶስት ዓመት የማይበልጥ እንዲሆን በህግ ይደነገጋል።

በሥልጣን ዘመኑ በጥቂቱ ከላይ ሲልም ሁሉም የሽግግር መንግሥት አካሎች በተስማሙበት ህግ እየተመራ ጊዜው ሲያበቃ በተመሰረቱት የሕዝብ ተቋማት አማካኝነት ዲሞክራሲያዊ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲመሰረት አስደርጎ በሰላማዊ መንገድ ሥልጣኑን ያስረክባል። ዘላቂ ሰላምና አስተማማኝ ሰርዓትም ይፈጠራል።

ከዚህ ውጭ ግን ከፊት ለፊት ያሉትን አንጋፋ የወያኔ ወንጀለኞችን ሰዎች ገለል ሰላሉ ተረኛው አካል በማጭበርበርና ስሙን ከኢህአዴግ ወደ ብልጽግና ፓርቲ ቀይሮ የተለወጠ መንግሥት ያለ ማስመሰል ጊዜው ያለፈበት የሌብነትና የውንብድና መንገድ ነው። መግቢያው ላይ እንደተጠቀሰው ወታደራዊ አምባገነን በ 1966 ለውጥ 'ከጦር ኃይሎች፣ የፖሊስና ብሄራዊ ጦር' ወደ 'ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት' ከዚያም ወደ 'ኢሠፓአኮ' ቀጥሎም 'ኢሠፓ' በሎ ስሙን በመቀያየር የመንግሥቱ ኃይለማርያም ወታደራዊ አምባገነናዊ አገዛዝ ጋር የተመሳሰለው ህወሃት / ኢህአዴግ አሁን ደግሞ ብልጽግና ፓርቲ ብሎ ከሚቀያይረው የጥፋት መንግሥት ጋር ምንም ልዩነት የለውም። ብልጽግና ሰለተባለ የ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አገዛዝ ስርዓቱና የሰርዓቱ አገልጋይ ተቋማት መች ተለወጡ? መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ ከመሆን በቀር።

<u>ማጠቃለያ</u>

እጅግ የሚያሳዝነው ከአንዴም ሁለቴ የሚታለለው 'አገር ወዳድ' የተባለው ክፍል ማጨብጨብና 'አብይን አላሰራ እኮ ያሉት 'እነ እከሌ ናቸው' የሚል ተልካሻ ምክያት በማቅረብ ለባለተረኛው የሚያገብድደው ክፍል ነው። በየቀኑ በአማራውና በአገው ሕዝብ ላይ ምን አይነት የግፍ ጭፍጨፋ እየተካሄደና ከኖሩበትና ከያሉበት እየተፈናቀሉ ባሉበት ወቅት ከገዳዮች ጋር እናብር የሚለው የአድር ባይና ሆዳም እሩጫ ነው። ዛሬ ኢንቨስትመንት ላይ የሚሯሯጠው አድር ባይ ስብስብ ሰለ ሕዝቡ መች ግድ አለው? ከገዳይና ካስገዳይ ጋር 'ቢዝነስ' ሊሰራ እየዋተተ ይገኛል። ይህ እጅግ አሳፋሪ ተግባር ነገ በታሪክ ፊት የሚቀርብ አሸማቃቂ ታሪክ መሆኑን ማስታወስ ይገባቸዋል፡፡

ሰለሆነም የተለያዩ ስብስቦችና ፓርቲዎች ብልጽግና ፓርቲ በሚወረውርላቸው ፍርፋሪና የፓርላማ ወንበር ችሮታ ተቋዳሽ ሊሆኑ እያነፈነፉ ታማኝነታቸውን እያሳዩ ሲገኙ፣ ሀገሪቱ ውስጥ ቀን በቀን ሰው በጥይት ይገደላል፣ በካራ ይታረዳል፣ ቤተክርስቲያን ይቃጠላል፣ ህዝብ ይፈናቀላል፣ ይዘረፋል። ይህ ሁሉ ድርጊት አብይ በወያኔ ብቻ እያሳበበ ሲነግራቸው አሜን ብለው የሚቀበሉ አድርባይና ነገ ጥቅም እናገኛለን ለሚሉ ጉዳያቸውም አይደል። ፍትሕ ተቀብራ ከገዳይ አስገዳይ ጋር መተባበርና በደጋፊነት መቆም በአገር ላይ ዋጋ ያስከፍላል፡፡ በሕዝብ ትግል ላይ ዋጋ ያስከፍላል፡፡

መቼ ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ መልስ የሚያገኘው? ባለተረኛው አገዛዝ መርጦ ባስቀመጠው ምርጫ ቦርድ ተብዬው? መከላከያው፣ ደህንነቱና ፖሊሱ የባለተረኛው በሆነበት ዘመን? የሀገሪቱን ሀብት የባለተረኛ በሆነበትና እየሆነ ባለበት? ፍትህ አፈር ብይ ተብላ በተቀበረችበት? ህዝብን በክልል ከፋፍሎ የሚያጋጨው የዘር ፖለቲካ ሕገ መንግሥት ሳይቀየር? እረ ቀልዱ ቢቃ!

የአብይ አገዛዝ የተለሳለሰ መስሎ የሚታየውና "ቅዱስ" የሚመስለው በግርግር ራሱ ባስቀመጠው ምርጫ ቦርድ አማካኝነት የግንቦቱ ምርጫ ተካሂዶ ' የሕዝብ ተመራጭ ጠ/ሚኒስትር' እስኪባል ድረስ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ እኔ ነኝ ያለ ፍጹም አምባገነን፣ ጨካኝነቱንና ባለተረኛነቱን የሚያሳይበት አረመኔነቱን እንደሚያሳየን ካሁኑ ልንገነዘበውና ልንጠነቀቅበት ይገባል፡፡ ከተኮሎኮሉት ተቃዋሚዎች ውስጥ እነኢዜማን አይነቱን እና ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸውን 'በተቃዋሚ' ስም ኮልኮሎ እንደወያኔ ጨዋታውን ይጀምራል፡፡ ያኔ የነሽመልስ አብዲሳን፣ ታዬ ደንድዓን፣ ለማ መገርሳን ስራ በተግባር እየተተገበረ ሲሄድ መዘግየታችን ግልጽ እየሆነ ይሄዳል፡፡ አካሄዳቸው ሁሉ ወደዚያ እያመራ መሆኑን ቢነግሩንም አልገባ ያለን ይመስላል፡፡ እነ እስክንድር ነጋ ይህን ተገንዝበው ነው ሲናገሩና ሲታገሉ 'በሽብርተኛነት' ተወንጅለው ቃሊቲ የተወረወሩት እንጂ ምንም አይነት ወንጀል ሰርተው አይደለም፡፡ ፍትህና ታሪክ ግን ነጻ ያወጣቸዋል፡፡ ነግ ሌላውም የአብይን አገዛዝ የሚቃወም ሁሉ እንደእነ እስክንድር ቃሊቲ እንደሚወረወር የማይቀር ነገር ነው፡፡

ይልቁንስ ተወደደም ተጠላም የሕዝብ ጥያቄ በተዳፈነና በጊዜያዊ ድራማዎች በተጭበረበረ ቁጥር የሕዝብ ቁጣ እያየለ፣ ስር እየሰደደ በሕዝባዊ አመጽና ቁጣ መመለሱ አይቀርም! ያኔ ይህን እድል ላልተጠቀማችሁበት ሁሉ ወዮ! የጊዜ ጉዳይ ነው!

ትላንትም ዛሬም የሽግግር መንግሥት ምስረታ የሕዝብ ጥያቄ ነው!

ኢትዮጵያ በልጆቿዋ አንድነትና ትግል በነጻነቷ ተከብራ ትኖራለች!